የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር ኦ1162/11/841
ቀን ጥር 04 2015

**ለኢትዮጵያ ነጻነት ፓርቲ (ኢነፓ)**

**አዲስ አበባ**

የኢትዮጵያ ነጻነት ፓርቲ (ኢነፓ) ሚያዝያ 2 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ የፓርቲ አባላት ያልሆኑ በልመና ተግባር የተሰማሩ በአበል ክፍያ በጉባኤው ላይ እንዲሳተፉ ማድረጉን እና የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ለጉባኤው ቀርቦ ሳይጸድቅ ፓርቲው ደንቡ ቀርቦ እንደጸደቀ በማስመሰል ለቦርዱ የሰጠውን የተሳሳተ መረጃ መሰረት በማድረግ ፓርቲው ከሀምሌ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ መታገዱን በመግለጽ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 98/3/ መሰረት መከላከያውን እንዲያቀርብ ቦርዱ በሀምሌ 14 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር አ1162/11/641 በተጻፈ ደብዳቤ ለፓርቲው አሳውቋል፡፡

ፓርቲው በሀምሌ 21 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር የኢነፓ/231/2014 በተጻፈ ምላሽ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠናቀቅ አካባቢ በልመና የሚተዳደሩ የተባሉትና የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ሰዎች አዳራሹ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ስለነበር፣ ዕለቱም ዕሁድ እንደመሆኑ በአዳራሹ ያለው የሙዚቃ ድምጽ ጎላ ብሎ ከመሰማቱ እና ለጉባኤተኛው ዳቦና ውሃ ተጭኖ መግባቱን ተመልክተው መምጣታቸውን፣ አስተባባሪዎች እነዚህ ሰዎች ወደ አዳራሹ እንዳይገቡ ሲከላከሉ እንደነበር፣ የጉባኤው መንፈስ እንዳይታወክም የተወሰኑት እንዲገቡ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ የጉባኤተኛ ቆጠራ ከተደረገ በኃላ የጉባኤተኛ ቁጥር የጨመረው አርፍደው የገቡ አባላት ስለነበሩ ነው፡፡ በተጨማሪ ጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ለመጡ አባላቶቻችን አበል መክፈላችን የተለመደ አሰራርና የሚካድ አይደለም ሲል የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ በሚመለከት የፓርቲው



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ +251 115 153468
ፋክስ +251 115 510025

ፌስቡክ /national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር @NEBEthiopia
ኢሜይል contact@nebe.org.et
ድረ-ገጽ www.nebe.org.et

ሲቀመንበር ጉባኤው ደንቡን እንዲያጸድቅ ሲጠይቁ ደንቡ በዝርዝር ይቅረብልን የሚል የአካሄድ ጥያቄ ባለመነሳቱ እጅ በማውጣት በተሰጠ ድጋፍ መጽደቁን ገልጸዋል፡፡

ቦርዱም ጉዳዩን ከህጉ አንጻር መርምሯል፡፡ ፓርቲው በጽሁፍ ያቀረበው መከራከሪያ በሚያዝያ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የተሳተፉ የፓርቲው አባላት ያልሆኑ ግለሰቦች በዕለቱ በአዳራሹ ውስጥ በነበረው የሙዚቃ ድምጽ ጎልቶ መሰማት እና ዳቦና ውሃ ለጉባኤተኛ ሲቀርብ አይተው ከአካባቢው ተሰባስበው የመጡ እንደሆነ አስረድቷል፡፡

የቦርዱ ታዛቢዎች ያቀረቡት ሪፖርት የሚያስረዳው በዕለቱ ጉባኤው በተዘጋጀበት አዳራሽ የሙዚቃ ሥነ-ሥርዓት የነበረው ከጠዋት 4:00 ሰዓት ጠቅላላ ጉባኤው እስከሚጀመርበት 6:25 ሰዓት መሆኑን፤ ዳቦና ውሃ ለጉባኤተኛው የቀረበው ደግሞ ጉባኤው ወደ መጠናቀቂያው በደረሰበት ከቀኑ 8:00 ሰዓት አካባቢ መሆኑን፤ በጉባኤው አጀንዳ መሰረትም የመክፈቻ ንግግር፤ የክብር እንግዶች ንግግር፤ የአስመራጮች ኮሚቴ ምርጫ፤ የስራ አስፈጻሚ ምርጫ እና የማዕከላዊ ኮሚቴ ምርጫ ለማከናወን የወሰደው ጊዜ ከቀኑ 6:25 ሰዓት እስከ ጉባኤው እስከተጠናቀቀበት 9:00 ሰዓት ድረስ መሆኑን፤ ጉባኤው ተጀምሮ እስከተጠናቀቀበት ሰዓት ቢያንስ በፓርቲው የታመኑት የፓርቲው አባል ያልሆኑ ግለሰቦች በጉባኤው የታደሙ እና የተለያዩ የጉባኤው የምርጫ ሂደቶች ውስጥ ሲሳተፉ እንደነበር ነው፡፡ በመሆኑም ቦርዱ ፓርቲው ከዚህ አንጻር ያቀረበውን መከላከያ አልተቀበለውም፡፡

የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ በሚመለከት ሊቀመንበሩ ጉባኤው ደንቡን እንዲያጸድቅ ሲጠይቁ ደንቡ በዝርዝር ይቅረብልን የሚል የአካሄድ ጥያቄ ባለመነሳቱ እጅ በማውጣት በተሰጠ ድጋፍ ጸድቋል በማለት ፓርቲው ያቀረበው መከራከሪያ በወቅቱ ጉባኤውን የታዘቡት የቦርዱ ባለሙያዎች የደንብ ማሻሻያ አጀንዳም ሆነ በጉባኤ የጸደቀ የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ አለመኖሩን ነው በሪፖርታቸው የገለጹት፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንጻር የቀረበውን መከላከያም ቦርዱ አልተቀበለውም፡፡

የፖለቲካ ፓርቲ ማለት ዜጎች ተደራጅተው የሚመሰርቱት የፖለቲካ ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ፤ በክልል ወይም ከክልል በታች ባለ ደረጃ በምርጫ

የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ተቋም እንደሆነ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 2/13/ ይገልጻል፡፡ ይህ ተቋም ወይም ድርጅት፤ የፓርቲ ሃላፊዎች እና አባሎቻቸው በዋናነት በመልካም ሥነ-ምግባር፤ በሃላፊነት እና በተጠያቂነት ስሜት ህግ አክብረው ይንቀሳቀሳሉ የሚል መሰረታዊ መርህ እና የህግ ግዴታ መኖሩ ዕሙን ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ፓርቲው ከፈጸማቸው ጥፋቶች ዓይነት የፓርቲውን ደንብ በተመለከተ ለጉባኤው ቀርቦ እንደጸደቀ አድርጎ ለቦርዱ መግለጹ በአዋጁ 1162/2011 አንቀጽ 79/3/ መሰረት ሀሰተኛ መረጃን ሆን ብሎ ለቦርዱ በድጋሚ መስጠቱን ያሳያል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 98/1ሠ/ የፖለቲካ ፓርቲው በማጭበርበር ወይም እያወቀ ወይም ማወቅ የተገባው ሆኖ ሳለ አሳሳች መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ ከሆነ ወይም በአዋጁ መሰረት መረጃ ሲጠየቅ የሀሰት መረጃ ለቦርዱ የሰጠ እንደሆነ ቦርዱ ፓርቲውን ከምዝገባ ሊሰርዝ እንደሚችል በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ቦርዱ ፓርቲው በፈጸማቸው ጥፋቶች ምክንያት ከምዝገባ እንዲሰረዝ ወስኗል፡፡

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board